በአዲስ አበባ የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ

እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የዋጃት ቤተ ክርስቲያን በስሙ ማመንን መሠረት ጉልላት አድርጋ ከተቋቋመችበት ጊዜ ጀምሮ ሥራዋ ያልተጣታ ዓላማዋ ያልታጠፈ ቢሆንም፥በዘሯ መካከል እንክርዳድ፣ በማኅበሯም ውስጥ የሚያሰናይ ምክንያት አልታጣም፥ ስለዚህም ወልድ ዋሕድ የሚሰውን ቃል መሠረት አድርጋ አንድ እግዚአብሔር ማለትን በአንድ ሃይማኖት ፤ በአንድ ጥምቀት የምትሰብክ ስትሆን ከመጀመሪያው ጀምሮ ጦርነት አልጠፋላትም ፤ በየጊዜውም መለየት እያተፈጠረ እየጸና ስለሔደ አራት ኛው መቶ ዓመቱ ምሕረት ሦስት ታላላቅ ጉባኤዎች ለመታሰቢያነት ትቶ አልፎ አል እነዚህም ጉባኤ ኒቅያ ፥ ጉባኤ ቁስጥንጥንያ፤ ጉባኤ ኤፌሶን ናቸው ።

ይህም ሳያግድ ቀርቶ በአምስተኛው መቶ ኢጋማሽ ላይ ቤተ ክርስቲያን ከሁለት ተከፈለች ፤ በስባተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት አጋማሽ ላይም ከክርስትና ወይም ከይሁድና ያልሆነ አንድ እግዚአብሔር ማለትን ብቻ በቃል የሚሠነዝር ሌላ የቤተ ክርስቲያን ተቋዋሚ ኃይል ወይም ክፍል ተነሣ ፤ ይህም ተቃዋሚ ኃይል ሁለቱንም የቤተ ክርስቲያንን ክፍሎች አጣምሮ የሚመታ ሆነ፥ያም ሆኖ ሁለቱም የቤተ ክርስቲያን ክፍሎች የየግል ዓላማቸውን እያሰፉ ፤ ጥላቻን እያበረቱ ከመሔድ በቀር አንድ ሆነው ጠላትን ለመቋቋም አልፈለጉም በሽታውም ፈውስ ሰለ አጣ በአሥረኛው መቶ ዓመተ ምሕረት አጋማሽ ላይ ሌላ መለያየት ተደረገ ፤ ከዚህም የሚበልጥ በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አራተኛ ልዩነት መጣ ፤ በዚህ ዓይነት ሊመለክቱት ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ በአራት አጠቃላይ ጎድ ተከፍላ ትገኛለች ፤ ይህ መለያየት ቤተ ክርስቲያንን ከየክ ፋፈለ ከመሔዱም በላይ ዓለም የሃይማኖት ነገር በጉዳያቸን ውስጥ አይግባ እስከ ማለት እንዲደርስና ከዚያም አልፎ እግዚአብሔር የለም ወደሚለው ስንፍና እንዲያመራ አድርጎታል ፥ ይህም በክርስቲያኖች ልቡና ብርቱ መቆርቆር ስለ አሳደረ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ አንድ እንሁን የሚለው የተስፋ ጭላንጭል መታየት ጀምሯል። ይህም ተስፋ ለዐበይት ጉባኤያት ልደት ምክንያት ሆኗል ።

በዚህ መሠረት በ፲፱፻፺፯ ዓ ም፥ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋባዥነትና አስተናጋጅነት በኢትዮጵያ አዲስ አበባ በአፍሪቃ አዳራሽ ተደርጓል ፤ እነዚህም ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አካል ፥ አንድ ባሕርይ ነው በማለት የሚተባበሩት የኢትዮጵያ የእስክንድርያ፥ የሶርያ፥ የአንጾኪያ ፤ የአርማንያ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ።

ዓለም፥ የሃይማኖትን ጉዳይ ራቅ ፤ ፈቀቅ ፤ ገለል አድርጎ ለምድራዊ ኑሮ ለኃላፊው ሥራ በሚጣደፍበት ጊዜ ሥጋዊው ይለ መንፈሳዊ ሕይወት፥ ምድራዊው ይለ ሰማያዊ

ሀብት ተሊየይዎ ሊኖር የማይችል ፡ በጠቅላላውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ፡ በእግዚአ ብሔር መንፈስ የማይመራ ሕይወት ከንቱ መሆኑን ኢጎብቀው የተመለከቱት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዓላማቸውን ወስነው፡በእውነተኛው ሃይማኖት ጸን ተው ስለሚሠሩና ስለሚመሩ ለኦብያተ ክርስቲያናት ጥላ ከለላ ሆነው ተሾኙ ፤ይልቁ ንም ከኢትዮጵያ በቀር አራቱ ኦብያተ ክርስቲያናት በጠላት ተከበው የሚኖሩ ስለሆነ ኢትዮጵያ ለጉባኤያቸው ታላቅ ተስፋ ሆና ተገኝታለች ።

በዚህ ምክንያት የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ኦብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ሥራ ውን በኃይለ ሥላሴ በሰላም በፍቅር ጀምሮ በኃይለ ሥላሴ በሰላም በፍቅር ጨረሰ ፤ በጉባኤው ውሳኔ ም የሃይማኖት ጠባቂ የሃይማኖት ጋሻ የለሚውን ከፍተኛ ስም ልጄ ንሆይ ሰጠ፡ ከዚህ ቀጥሎ ጉባኤው የተከፈተበትንና የጉባኤውን ውሳኔ እንመልከት ።

ከኤፌሶን ጉባኤ ወዲህ አህጉረ ዓለም ነክ የኦብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በእጎት ማማኞች ኦብያተ ክርስቲያናት መክክል ሲደረግ ፡ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነ ው ፡ ስለዚ ህም ይህ ጉባኤ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ባንድ በኩል በቀድሞ ጊዜ ዐበይት ጉባኤያትን ከሰበሰቡ ደጋግ ነገሥታት ሲያስተባብራቸው ፤በሌላ በኩል ደግሞ ከፍ አድርጎቸው ይገኛል ።

ምክንያቱም እነዚያ የቀድሞቹ ነገሥታት በጉባኤ የሰበሰቡ በክፍለ ግዛታቸው ያሉትን የኦብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ነው ፤በሰላማዊ መሪ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጥላ ሥር የተሰበሰቡ የዓለም ኦብያተ ክርስቲያናት ግን፡ በጀንሆይ እውነተኛ ሃይማኖት በጀንሆይ ንጹሕ ፍቅርና በተቀደሰ አመራር እንጂ በተገዢነት አይደለም ፤እነዚህ ኦብ ያተ ክርስቲያናት ምንም እንኳን ከረዥም ጊዜ ጀምሮ የሃይማኖት መሠረት ያላቸው ቢሆኑና ያንኑ እጽንተው የኖሩ ቢሆኑም ኑሯቸው በተኩላ መክከል በመሆኑ ብዙ የት ግል ኑሮ እንዳለባቸው አይጠረጠርም ፤ ስለዚህ ለጥ ቂት ጊዜም ቢሆን ከዚያው ወጣ ብለው በጎና መንግሥት በሰላማዊና በሃይማኖታዊ ንጉሠ ንግሥት የምትደገፍና የም ትጠበቅ ቤተ ክርስቲያን ማየታቸው መንግሥቱ ስማያትን በዐረቦን እንዳዩአት ያህል የሚያስቆጥር ነው ። በአንጻሩም ስብሰባቸው ለኢትዮጵያ በረከትን ሰጥቷል ።

ይህ ሁኔታ ጃንሆይን ከባለታሪኮች በላይ ፤ታሪካቸውንም ከታሪክ በላይ፡ ስለሚ ያደርገው ጉባኤው ለትውልድ የማይረሳ የድንቅ ድንቅ ነው ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የምሥራቅ ተዋሕዶ አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪ ዎችን ጉባኤ በከፈቱበት ዕለት ያደረጉት ንግግር ።

ብፁዓን ወቅዱሳን አባቶች ።

የቤተ ክርስቲያን አባቶች ለአንድ ዓላማ በዚህች በታሪካዊት አገራችን በጎብረት መገኘታችሁ፡ ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም፡ ሶበ ይሄልዉ አኃው ኅቡረ፡ ያለው የዳዊት መዝ ሙር ሁልጊዜም አዲስ መሆኑን ያስገነዝበናል ።

ቅዱሳን አባቶች ፡

በጥልቅ እንደምታውቁት ሁሉ የቤተ ክርስቲያን አንድነት በፈቃደ እግዚአብሔር የተደገፈ ነገር ስለሆነ ታላቅ አብነት በመሆኑ ለሰው ልጅ ጠቅላላ ጎብረት ሆነ ። ወ ይም ለልዩ ልዩ ሃይማኖት ተከታዮች አንድነት ደገፋ እንጂ ዕንቅፋት ሊሆን አይች ልም ። ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሐዋርያት ጀምሮ ከዚያም በኋላ የነበሩት

ሐዋርያዊ የሥራ አመራርንና የመንፈሳዊ ትምህርት አሰጣጥ ፤ ጉዳይ ሁሉ በሲኖዶስ በጎበረት ይሠሩ እንደነበረ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሰፊው ያስረዳል ። በዚህ አካሄን ተግናኝተው ፡ ተወያይተው የጋራ ችግርን ማስወገድ ከዕለት ወደ ዕለት እርምጃቸውን ሊቀጥሉ ችለው ነበር ።

ብፁዓን ወቅዱሳን መሪዎች ፡ የተከበራችሁ አባቶች ፡ ወደዋናው ከተማችን እንድ ትመጡልን ጥሪያችንን ስንልክላችሁ የአናንቱ እዚህ መገኘት በተለይ የቤተ ክርስቲ ያንን አንድነት እንደዚሁም የሰው ልጆችንም የአንድነት መሠረት እንደሚደግፍ ተ ስፋ በማድረግ ነው ።—

ዛሬ ባለንበት ዘመን እንኳን የሰላም ምንጭ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን የዓለም መንግሥታትም ቢሆኑ የቀድሞውን የመሊያየት መንፈስ ትቶ በጎብረት መሥራት የጋራ ችግርን በማስወገድ ነፍ ያለ ጥቅም እንደሚሰጥ ተረድተው በሚያስደስት አካሄን ተግ ባራቸውን ሲፈጽሙት ይገኛሉ ። ይህ ተባብሮ መሥራትና የጋራ ችግርን ማስወገድ ጥንቱኑ ከቤተ ክርስቲያን የተወለደ ስለሆነ ፡ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ተግባር ውጭ ልት ሆን አይገባትም ።—

ኢትዮጵያዊት ቤተ ክርስቲያን እንደ ሃይማኖታችን ጥንታዊት ናት ። ታሪክዋም በማ ያወላውለው በሕዝብዋ የእምነት ጥንካሬ ዝና በስማዕታትዋና በቅዱሳንዋም ገድል የተሞላ ነው ። የሕዝባችን ታሪክ ከቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ጋራ ተያይዞ የኖረ እንደ መሆኑ መጠን ቤተክርስቲያናችን ብሔራዊ አንድነታችንን ያጠነከረችና የመንፈስ ብርታ ትም ለሕዝባችን የሰጠች ናት ።—

ኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይ አገር ናት ። ከ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በየጊ ዜው ከግብፅና ከሶርያ እንዲሁም ነስሌሶች አህጉር የመጡትን አባቶች ስትቀበልና ስታስተናግድ የኖረች አገር መሆኗን ለማስታወስ ያህል ቅዱሳን ብለን የምናከብራቸውን አባቶች ተሰዓቱ ቅዱሳንና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስንን ለአብነት እንጠቅሳለን ። እነ ዚህም ቅዱሳን አባቶች በማስተማር ገዳማትን በመመሥረት ለሀገራችን የሰጡት መን ፈሳዊ በረከት ከፍ ያለ ስለሆነ ለስማቸው መጠሪያ የገዳማትና የአብያተ ክርስቲያናት ሐውልት ቆሞላቸዋል ።—

በጥንት ዘመን የቤተ ክርስቲያን እምነት አንድ በነበረበት ጊዜ ሀገራችን ከቢዛንስ ነግሥታት ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበራት ። የክርስቲያን አህጉርን ክርስቲያን ያልሆኑ ገዥዎች ቁንበር ተጭኗቸው በነበረበት ጊዜም በብዙ የሚቆጠሩ ደሃይማኖት ስደተኞችን አስጠግታለች ።

እንደዚሁም ቀደም ብሎ የእስላም ሃይማኖት መሥራች ተከታዮች ስለ ሃይማኖታቸው በተሰደዱ ጊዜ፡ እነሱንም ተቀብላ መጠጊያ ሰጥታቸዋለች ። ሀገራችን በሰሚናችንና በም ሥራቃችን ካሉት ክርስቲያኖች ወንድሞቻችን ጋር የነበራትን ግንኙነት ለማስፋፋት ያዳገታት ግን ፤ የቅርብ ጎረቤቶቻችን የሆኑት አህጉር ክርስትናን ከለቀቁ በኋላ ነበር ። ሆኖም ኢትዮጵያ ሀገራችን የክርስትና ደሴት እንደመሆኗ ክርስትናን ከተቀበለችበት ዘመን ጀምሮ የክርስቲያንነት እምነቷን ሳታጓድል ከጥንት ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላት ግንኙነት

እንዳይቋረጥ ከመጣጣር አልቦዘነችም ። ቤተ ክርስቲያን የእስክንድርያው የቅዱስ ማር ቆስ ልጅነቷን አጽንታ መኖርዋንስ የማያውቅ ማን ይገኛል? ዛሬ በጎበረት ተሰብስበን ለመወያየት ያበቃን የዚያ የጥንቱ አንድነታችን ፍሬ ነው ። በክርስትና እምነት እናንተ ከመጣችሁባቸው ልዩ ልዩ ሀገሮች ጋር ያለንን ግንኙነት ለመጠበቅ በብዙ የሠሩት አባቶቻችን የኢትዮጵያ ነገሥታትና ሕዝብ በመሆናቸው ያለፉትንም ፣ ያሉትንም ሳና መሰግናቸው አናልፍም ።—

ቅዱሳን መሪዎች ፣

ወደ ሀገራችንና ወደ ቤተ ክርስቲያናችን እንኳን በደኅና ገባችሁ የምንላችሁ በጣ ም ደስ እያለን ነው ። የእናንተ መምጣት ጥንታዊ የሆነውን ቅዱስ ስሜት ይዞልን መጥ ቷል ፣ የእናንተ እዚህ መገኘት መላው ሕዝበ ክርስቲያን አንድ ይሆን ዘንድ በሰው ሁሉ ልብ ለተፀነሰው ምኞት ዋስትናና ምሳሌ ይሆናል ።—

ንጉሠ ነገሥት ከሆንበት ጊዜ ጀምሮ ልንፈጽማቸው ከሚገቡን ግዴታዎች አን ደኛው በእምነት አንድነት ሲኖራቸው በሀገር ርቀት የተለያዩትን አብያተ ክርስቲያ ናት ማገናኘት እንደሆነ አምነን ፣ በአምላክ ርዳታ ይህንኑ ለመፈጸም ይህችን ዕለት ስን ጠብቅና የእግዚአብሔርን ቅዱስ ፈቃድ ደጅ ስንጠና ነበር ። ቀድሞውንም ከአንደኛው ጀምሮ እስከ ሦስተኛው ለተደረጉት የጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ሁሉ ጠሪ ዎቹ የቊስጥንጥንያ ክርስቲያናውያን ነገሥታት ነበሩ ። በዚህም እኛ ለቤተ ክርስቲያን ከገባነው ቃል ኪዳን ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ያገኘነው እምነት የሚመሰረትን አብያተ ክርስቲያናት አገናኝቶ በጎበረት እንዲሠሩ ማድረግ ነበረ ። የገባነው ቃል ኪዳን በዛ ሬው ዕለት ሲፈጸም በማየታችን እጅግ ደስ ብሎናል ።—

ሰው ያሰበውና የተመኘው ሲፈጸምለት ከማየት የበለጠ ደስታ ሊያገኝ አይችልም ። ስለዚህ እኛም ልንሠራው የሚገባንን ግዴታ በመፈጸማችን ፣ የተመኘነውና ያሰብ ነው በሥራ ላይ ውሎ በማየታችን፣ ለእግዚአብሔር ንዱሕ ምስጋና እናቀርባለን ። ኃይል የሚገኘው ከጎበረት የተነሣ ነው ። በጎበረት የሚሠሩትን በኔ ስም ሁለቱ ሦስቱ ቢሰበሰቡ እኔ በመካከላቸው እሆናለሁ ፣ የሚሹትንም ነገር እፈጽምላቸዋለሁ ሲል የተናገረው አምላክ ይረዳቸዋል ።—

አያሌ መቶ ዓመታት የአርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያኖቻችን ደንበኛ ግንኙነት ሳይኖራቸው ኖረ ዋል ። የስፋፊላቸው ምክንያት ቀዋሚ ፍሬ ነገር ያለው ሊሆን ወይም ላይሆን ይችላል ። የሆነ ሆኖ ለፖለቲካዊ ጠብ እንኳን ሰዎች በጉባኤ ተቀምጠው በሰ ላምና በወዳጅነት መንፈስ ፍቺ በሚፈልጉበት በዛሬው ዘመን አብያተ ክርስቲያናት በተ ለይ የሚያደርጉት ጥረት ከዚህ ያነሰ መሆን የለበትም ።—

ይህ ያለንበት ዘመን በመገናኛ ረገድ ከፍተኛ እርምጃ የተደረገበት ከመሆኑ የተ ነሣ የአንድነትና የመቀራረቢያ ዘመን ተብሎ ይጠራል ። ይሆነ በምናስብበት ጊዜ የስ ዊድን ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ዶክተር ናታን ሶደርብሎም የክርስቲያኖች ጠቅላላ ጉባኤ በእስቶኮሆልም ከተማ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ፲፱፻፳፫ ዓ ም ለመሰብሰብ እንዲ ችል ያደረጉት የቀዳሚነት ተግባራቸው ይታወሰናል ። አሁንም በቅርብ ባለፈው ጎዳር ወር በባቲካን ከተማ በብፁዕ ወቅዱስ ጳው ሎስ ስድስተኛ መንፈሳዊ መሪነት

የተሰበሰበው ከፍተኛ መንፈሳዊ ጉባኤ ያከናወነውን ሥራ በጥልቅ ተከታትለነዋል ። እውነት ነው፡ስለዚህ ጉዳይ የኢብያተ ክርስቲያኖቻችን መሪዎች በአሁኑ ስብሰባችሁ እን ዳችም ቁርጥ ውሳኔ እንድትሰጡ አይቻላችሁ ይሆናል ጉዳዩም ባንድ ወገን ወሳኝነት ብቻ የማይፈጸም ይሆናል ። ቢሆንም ዕርቅና ጎብረትን ሊያስገኙ የሚችሉት መንገዶችና ዘዴዎች ከእናንተ ከመሪዎቹ ሊገኙ እንደሚችሉ እምነት አለን ።—

ስለ ዓለም ሰላም መጽለይና መሥራት ክርስቲያናዊ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ በጉዳዩ አጥብቃችሁ እንደምታስቡበት በጉባኤው የንግግር ፕሮግራም ይታወቃል ፤ የሰው ልጅ በጥበቡ በሠራው መሣሪያ እንዳይጠፋ ታሳቅ ሥጋት በአስተዋዮች ልቡና ባደ ረበት ባሁኑ ሰዓት ፡ ምሕረት የሚገኘው በቤተ ክርስቲያን አማካይነት መሆኑን ሳይመለከ ተው የሚቀር የለም። ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ጋር በመተባበር ሊሠሩ ከሚገባ ቸው ሥራዎች አንዱ አይነተኛው ሥራ ይህ የዓለም ሰላም ጉዳይ መሆኑን ማሰብ ይገ ባል ። ክርስቶሳውያን ተብለን የርሱ ወገኖች ሆነን ሳለ በመለያየት እንደተጐዳን እና ስብ ።—

በንግግራችን መደምደሚያ የማኅበራዊ ኑሮን መሻሻል ጉዳይ እንጠቅሳለን ። በየት ኛውም ክፍለ ዓለም ቢሆን የሰው ልጅ ማኅበራዊ ኑሮ ሊደገፍ የሚችለው በቤተ ክር ስቲያን ነው ። በነ አድራጎት የሚሠራው ፡ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ የሚፈጸመው የሰው ልጅም በሥጋዊውና በመንፈሳዊው ረገድ እርምጃውን የሚቀጥለው የማኅበራዊ ኑሮ መሻሻል መልክ ያገኘ እንደሆነ ነው ።—

ቅዱሳን አባቶች ፡

የእናንተ ከዚህ መገኘት ለሀገራችንና ለሕዝባችን በረከት መሆኑን ስናስብ ዕድ ለኝነታችን ይሰማናል ። ሕዝባችንና ሀገራችን እንኳን በደኅና ከመሐከላችን የተገኛች ሁልን በማለት ደስታ ቸውን ይገልጣሉ ።—

እናንተ ቅዱሳን አባቶች የእግዚአብሔር ሐዋርያት እንደራሴዎች እንደመሆናችሁ ሕዝብና ክህናት ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ጥብቅ ግንኙነት እንዲኖራቸው ሰማ ድረግ እንድትችሉና ይህንንም በመፈጸም ላይ የጋራ ችግር ቢኖር ም በጎብረት ኢጥን ታችሁ ፍቱኑን መድኃኒት እንድታስገኙ በእምነት እንጠባበቃለን ።—

ልዑል እግዚአብሔር በኂቅያ ጉባኤ የተሰበሰቡትን ሦስት መቶ ዐሥራ ስም ንት ሊቃውንት እንደረዳ ለነርሱም እንዳበራላቸው እናንተንም ይርዳችሁ ። ዓይነ ልቡ ናችንንም ያብራልን ። ከየግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ንግግር ቀጥሎ ብፁዕ ወቅዱስ ሞራን ማር አግናጢዮስ ያዕቆብ የሚተለውን ተናገሩ ።

ብፁዕ ወቅዱስ ሞራን ማር አግናጢዮስ ያዕቆብ ፫ኛ የአንጾኪያና የመላው ምሥ ራቅ ፓትረያርክ ፡ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጉባኤውን በከፈቱበት ቀን ላደረጉት ንግ ግር የሰጡት መልስ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት
ቅዱሳን አባቶችና ወንድሞች ፡
የተወደዳችሁ ክህናትና ምእመናን ።—

በዚህ ዓይነት ዓለማ ከዚህ በመገኘታችን ከኃያሉ እግዚአብሔር ያለን ፍቅር በጣም ጥልቅ ነው። በልባችንም የሚሰማንን ደስታ ለመግለጥ ቃላት አናገኝለትም። ግርማዊ ጃን

ሆይ በዚች በተዋበች ከተማዎ አንድነት እንድንገናኝ በማድረግዎ የማይረሳ ዘለዓለማዊ ዕድል አጐናጽፈው፡ የግርማዊ ነትዎን ንግግር በአዳመጥን ጊዜ በ፲፱፷፭ ዓ ም በኒቅያ የተደረገው ሲኖዶስ ይታወሰናል ።—

በዚህ ጊዜ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ጉባኤውን ሲከፍት ለአደረገው ንግግር የአንጾኪያው ቅዱስ ኤዎስጣቴዎስ ንጉሡን በማመስገን መልስ ሰጥተዋል ፤ ሆኖም በቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ተቀምጠን የዚህ ቆዱስ ሰው ወራሽ ለመሆን የበቃን ነን ለማለት ባንችልም ይህን አስደሳች የሆነውን የግርማዊነትዎን ንግግር ተከትለን እነዚህን ቃላት ስንናገር እንደ ሕልም ይሰማናል ። ግርማዊነትዎ ይህን ታሪካዊ ጉባኤ / ኮንፈረንስ / በማዘጋጀትዎ በየነበሩባቸው ዘመናት ቤተ ክርስቲያንን በቅን ያገለገሉትና የረዱት የሃይማኖታውያን ነባሥታት እውነተኛ ተከታይ መሆንዎን አሳይተዋል ። ይህን ግርማዊነትዎ ያዘጋጀውን ጉባኤ፤ በማሰብ ለኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ፡ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጥልቅ ምስጋናችንን እንገልጣለን ።—

የእነዚህ የምሥራቅ እጎትማማቾች አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ኃላፊዎች መገናኘት ለአብያተ ክርስቲያኖቻችን አንድ ትልቅ ታሪካዊ እርምጃ ነው ። ምንም እንኳ አንድ ዓይነት ዓላማና እምነት ቢኖረንም እንደ አሁኑ በአንድነት ተገናኝተን ለመወያየት ለብዙ መቶ ዓመታት ዕድል አላገኘንም ። ነገር ግን አሁን እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በይሁዳ አንበሳ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አማካይነት አንድነት እንድናገኝ አስቻለን ። በእውነቱ ዝቅተኛው ራሳችን በቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ላይ ከተቀመጠበት ጊዜ ጀምሮ አብያተ ክርስቲያኖቻችን እንዲገናኙ መንገዱን እንዲከፍትልን እግዚአብሔርን ስንለምነው ነበር። ወዲያው እኛ እንደተሾምን ከሜትሮ ፖሊታን ወን ድሞቻችን ሁለቱ ኢትዮጵያን በጎበኙ ጊዜ ግርማዊነትዎን ይህን ነገር እንዲበረቱበት ለማነቃቃት በነሱ አማካይነት አንድ መልእክት ልከን ነበር ፤ አሁንም ግርማዊነትዎ በአርቆ አሳቢነት ይህን ኮንፈረንስ ጠሩ፤ እኛም የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚህ ነገር ከልብ ተደስተን ፡ በዚህ አጋጣሚ ጊዜ ግርማዊነትዎ እኛም በታላቅ አክብሮት የምንመለከትዎ የኢትዮጵያ መሪ መሆንዎን ለመናገር እንወዳለን ። ሁል ጊዜ በሥርዓተ ቅዳሴ ያችን ግርማዊነትዎን እናስታውሳለን ።—

ይህንንም በማድረግ በ፬ኛው መቶ ዓመት የነበሩትን ማር ሲቢሪዩስ ፡ ሙስ ባርኪፎ በ፲፪ኛው መቶ ዘመን የነበሩት ማር ዲዮናስዮስ ባርሳሊቪ የመሳሰሉትም የታወቁ አባቶችን ትምህርት እንከተላለን ። እነሱም በሥርዓተ ቅዳሴያችን የኢትዮጵያን ነባሥታት እንድናስታውስ ከእኛ ጋር ይተባበራሉ ። ከእኛም ጋር አንድ ዓይነት እምነትን ይሳተፋሉ ፡ ይተባበራሉ ፤ አብያተ ክርስቲያናችን በአጭሩ በ፬ኛው መቶ ዘመን ጀምሮ በጣም የቀረበ ግንኙነት አላቸው ። የመጀመሪያ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ፍሬምናጦስ ከኛ መንበር፤ሥር ከሆነችው ከጢሮስ እንደመጣ እንተርካለን። ማር ያዕቆብ ባራድዮስ በ፯ኛው መቶ ዘመን ኢትዮጵያን ጐብኝቷል ። በዚህም ጊዜ ተሰዓቱ ቅዱሳን አገራቸውን ሶርያን ትተው ወደዚህ አገር መጥተዋል ። እኛም ይህችን ታላቅ አገር ሕዝቧንና ቤተ ክርስቲያኗን ለመጐብኘት በመቻላችን የሚሰማን ደስታ በጣም ከፍ ያለ ነው ።—

አብያተ ክርስቲያኖቻችን የተዋሕዶ ኦርቶዶክስ እምነትን ከአባቶቻችን ነው የወረሱት ። ነገር ግን በእግዚአብሔር መለኮታዊ የማዳን ኃይል ትርጉሙን ገልጠን ለማሳየት አልቻልንም ፡ በአጠባባችን ላሉት ኢአማንያን፤ አብያተ ክርስቲያኖቻችን የክርስቶስን ወንጌል በጣም እንዲያውቁት ለማድረግ ያልቻሉበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው ፤

እንግዲህ በዚህ ጉባኤ በመካከላችን የሚኖረውን አንድነት ማጠንከር ብቻ አይደለም ። ነገር ግን ሕዝባችን በእምነታችን የሚያድጉበትን መንገድ እንደ ነና መመርመር ያስፈልገናል ።—

ከዚህም ሌላ የክርስቲያን ምስክርነታችንን በዓለም መልካም ውጤትን ያሳይ ዘንድ ባንድ የጋራ ፕሮግራም ማስማማት አለብን። በዚህም ዓይነት ኃያሉ እግዚአብሔር በጉባኤያችን ለጥንታውያን አብያተ ክርስቲያኖቻችን አንድ መንገድ ይከፍትልን ፡የሚደረገውንም ሙከራ ይፈጽምልን ዘንድ እንለምነዋለን ።—

ለግርማዊነትዎ ፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ወንድሞቻችን የሶርያን ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ እናቀርባለን ። የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊኮስ ወንድማችንን ባስልዮስ አጌን ፩ኛ በዚህ ጉባኤ ከኛ ጋር ይገኛሉ ። እኝህ አረጋዊ የሽምግልና ጊዜያቸው ሳያግዳቸው ከሕንድ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የዚህ ጉባኤ ተካፋይ ሆነው በማየታችን ከፍ ያለ ደስታ ይሰማናል ። አሁንም በሕንድ የሶርያን ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ እንድናቀርብ ይፈቀድልን ፡

የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ ·

፩ኛ / ው ሳ ኔ ፡

እኛ ከመልእክተኞቻችን ጋር በዚህ ጉባኤ የተሰበሰብን የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የሆኑት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የሃይማኖት ጋሻ ብለን እውጀናል ።—

የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ

፪ኛ / ው·ሳኔ

እኛ ከመልእክተኞቻችን ጋር በጉባኤ ተሰብስበን የነበረን የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የተሳካ ውጤት ባስገኘው ጉባኤያችን መጨረሻ ነገሩን ላነሣሱትና በኢርቆ አስተዋይነት ጉባኤው እንዲደረግ ላስቻሉት ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በረከታችንን ስናቀርብ ደስ እያለን ነው ።

በዚህም ኢድራጎት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ የተመደበላቸውን ሥራ በማጠናቀቅ የሃይማኖት ጋሻዎች እየተባሉ የተጠሩትን ታላላቅና ቅዱስ መንፈስ ያደረባቸውን መሪዎች ልማድ ተከትለዋል ። ጉባኤው ይህንን ጉባኤ በማደራጀት ለደከሙት ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምስጋና ያቀርባል ። በዚህም ጉባኤ ላይ ስለ ተደረገው ም የተከናወነ ድርጅት ጽሕፈት ቤቱን ከመሪው ከክቡር ዋናው ጸሐፊ ጋር ያመሰግናል ።—

የውቢቱን ኢትዮጵያ መሬት ስለነበኙ ሃይማኖተኛውን ሕዝቡንም ስላወቁ የጉባኤው አባሎች በመላ ተደስተዋል ።—

በፍቅርና በወንድማማችነት ለኃያሉ እግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን ። በቅዱስ እግዚአብሔር መሪነት ይህ ጉባኤ ለአብያተ ክርስቲያኖቻችንና ለክርስትና እምነት መጠበቅ በደስታ የመሠረተውን መሠረት ለማፋፋትና ለማጠንከር ሌሎች ጉባኤዎች እንደሚከተሉት ጽኑዕ እምነታችን ነው ።—

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት

በምሥራቅ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ፍጻሜ ያደረጉት

የመደምደሚያ ንግግር ።

ብፁዓን ወቅዱሳን አርእስተ ሊቃነ ጳጳሳት ፤ አሁን በተናገራችሁት ምሥጢራዊ ቃላት ስትሠሩ በሰንበታችሁት መንፈሳዊ ውጤት ልቡናችን በደስታ ተነክቷል ። በእርግጥም በቅዱስ መንፈስ ተመርታችሁ ፍቅር አንድነትን ይዛችሁ እንደሠራችሁት በሥራችሁ ውጤት ዓለም ሁሉ ሊረዳ ችሏል ።—

የምሥራቅ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ እምነት እውነተኛ ሥርዓት ያላት እንደሆነች ዓለም ሁሉ ሊቀናባት የሚገባው በዚህ ሰሞን በጎበረት በፈጸማችሁት ነገር ነው ።—

« የሀገር ርቀት የሰውን ፍቅር አይከለክለውም » ብሎ ሰሎሞን እንደተናገረው የሀገሩን ርቀት የልባችሁ ቅርበት አጥፍቶታል ። ስለዚህ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ አሳቢ ሆናችሁ ተገኝታችኋል ። እኛም በበኩላችን ያሰብነው ሁሉ ተፈጽሞልን ይህን መልካም ውጤት ስናይ ለአምላካችን ንጹሕ ምስጋና እናቀርባለን ።—

በዛሬው ጉባኤያችሁ ውጤት ተመርኩዘን እናንተንና የቢዛንቲን ኦርቶዶክስ ክዚያም በኋላ ሌሎችንም አብያተ ክርስቲያናት ለመጥራት ዝግጁ መሆናችንን ስንገልጥ ላችሁ ደስታ ይሰማናል ። ይኸም ከሆነ በቅርቡ እንደምንገናኝ እምነታችን ፍጹም ነው ።ጉባኤው ሲከፈት እንደተናገርነው ሁሉ እየተግናኙ እየተመካከሩና እየተረዳዱ መሥራት ብዙ ጥቅም ተጎናጽፉበት፥ የዓለም ነገሥታት በብዙ መልክ ይፈጽሙታል ። እንግዲያውስ እናንተም ከዛሬ ጀምሮ መንገዱ ክፍት ነው ፤ ርዳታችንም አይቋረጥም ። የሀሳባችሁ ደጋፊ መሆናችንን ስንገልጥ ግዴታችን መሆኑን በማመን ነው ።—

በተለይ የምናመሰግናችሁ ሥራችሁ ንጹሕ መንፈሳዊ ሆኖ ከፖለቲካ የራቀ በመሆኑ ነው ። ወደፊትም የምናሳስባችሁ ቤተ ክርስቲያን ራሷ የሰላም ምሳሌ ስለሆነች በየትኛውም ዓለም ቢሆን በሰላማዊ መንገድ ብቻ መገኘት እንዳለባት ነው ። ወደ ዓለም ውስጥ ጉዞአችሁ ለትምህርትና ለስብከት ይሁን ፤ ስለ ሰውም ልጅ መብትና ስለ ዓለም ሰላም መጸለይ ግዴታችሁ እንደሆነ ስንገልጽ በሪፖርታችሁ ላይ እንደተረዳነው ግዴታችሁን በሚገባ እንደተወጣችሁት ነው ። የዓለም ሰላም ሊገኝ የሚችለው በጸሎት በእግዚአብሔር ቸርነት ነው ይህን አስተያየት ሥጋዊ ደማዊ የሆነ ሁሉ ሳይረዳው አይቀርም፥ አሁንም እግዚአብሔር የሥራችሁ መጀመሪያ ሆኖ እንዲአስፈጽማችሁ ውጤቱን በሥራ ላይ ለማዋል እንዲረዳችሁ እንመኛለን ።—